# የዕቃ ማስተላለፍና  ተዛማጅ የባህር ወደብ አገልግሎት ክፍያን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

## መግቢያ

አገራችን እ.ኤ.አ አፕሪል 13/2002 ከጅቡቲ መንግስት ጋር በወደብ አጠቃቀም ዙሪያ በፈረመችው ስምምነት መሠረት የጅቡቲ የባህር ወደብ የአገሪቷ ዋነኛ የገቢና የወጪ ዕቃ መነሻና መድረሻ በማድረግ ላለፉት በርካታ ዓመታት እየተገለገለች መሆኗ ይታወቃል፡፡

በሁለቱ አገራት የተፈረመውም የወደብ አጠቃቀም ስምምነት ስምንት ክፍሎች የያዘ ሲሆን በዋናነት አገሮቹ ያላቸው መብቶችና ተነፃፃሪ ግዴታዎችን ያካተተ ነው፡፡በስምምነቱ ክፍል ሁለት አንቀጽ 5 /4/ መሰረት በጅቡቲ ወደብ ለተሰጠ የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ያገኘው የኢትዮጵያ ዕቃ አስተላላፊ ለተሰጠዉ አገልግሎት የወጣዉን ወጪ እና የተሰጠውን አገልግሎት ዝርዝር የሚያሳይ በሁለቱም ወገን የታመነበት የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ኢንቮይስ /Invoice/ ከጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ /ትራንዚተር/ በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ አገልግሎቱን ለሰጠው የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ ክፍያን እንደሚፈጽም / The Ethiopia side has agreed to effect the payment for the service provided by the Djibouti maritime transport auxillaries with in 15 days after the submission of the appropriate document/ በሚልበግልፅ አስቀምጧል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰዉ ይህ የድህረ ክፍያ ሥርዓት በሁለቱ አገራት የወደብ አጠቃቀም ስምምነት ላይ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም የሁለቱ አገራት ዕቃ አስተላላፊዎች በሚፈጽሙት የሥራ ውል መሰረት የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊዎች ለኢትዮጵያውያን አቻዎቻቸው እስከ 90 ቀን ድረስ ሊደርስ የሚችል የዱቤ አገልግሎት እየሰጧቸው እንደሆነ ያለዉ የሥራ ልምድ ያሳያል፡፡

ይህ የዱቤ አገልግሎት በተዋዋዮች ነፃ ፍላጎት ላይ የተመሰረተና ለሁለቱም አገራት  ዕቃ አስተላላፊዎች ሥራን ከመፍጠር፣ደንበኛን ከማብዛት እንዲሁም ገንዘብን ከማንቀሳቀስ አኳያ ጥቅም ያለው ነው፡፡ ሆኖም ለተሰጠው ዕቃ ማስተላለፍ የዱቤ አገልግሎት ክፍያ  በጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊና በኢትዮጵያ ዕቃ አስተላላፊ ፍላጎት መሰረት በዉሉ በተጠቀሰው ጊዜ እየተፈጸመ አይደለም፡፡ እንዲሁም የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊዎች በድንበር ዘለል የዕቃ ማስተላለፍ ሥራ ላይ ለመሠማራትና ለመሥራት ፍቃድ ካልተሰጣቸው ከኢትዮጵያ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት

አስፈፃሚዎች ጋር የሥራ ውል ገብተው መሥራታቸው የአገልግሎት ክፍያቸዉ አሰጣጥ በተመለከተ ህጋዊ በሆነ መንገድ አለመፈፀሙ ሁለቱ አገራት የተስማሙበትን የድህረ ዕቃ ማስተላላፍ አገልግሎት ክፍያ ስምምነትን ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡

ይህንኑ ተከትሎ በጅቡቲ ወገን እ.ኤ.አ ኖቬምበር 25/2013 የጅቡቲ ወደብ ባለሥልጣን ለኢትጵያ ማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን በፃፈው ደብዳቤ በጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊዎች ለኢትዮጵያ ዕቃ አስተላላፊዎች የሚሰጠው የዕቃ ማስተላላፍ ክፍያ በሁለቱ አገራት የወደብ አጠቃቀም ስምምነት ላይ በተገለፀው ቀን ውስጥ እየተከፈለ እንዳልሆነ ገልጿል፡፡

በመሆኑም ቀድሞ የነበረውን የድህረ የትራንዚት አገልግሎት ክፍያን ወደ ቀድመ የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ ሥርዓት የሚለወጥ መመሪያ በማዉጣት ተግባር ላይ እንዲውል የተወሰነ መሆኑን አሳውቋል፡፡

ይሁን እንጂ በጅቡቲ ወደብ ባለሥልጣን የአከፋፈል ሥርዓቱ የተለወጠበት አካሄድ የሁለቱ አገራትን የወደብ አጠቃቀም ስምምነትን ማሻሻል በተፈለገ ጊዜ መከተል የሚገባን ሥርዓትን ያልተከተለ ነው፡፡

ይህንንም ተከትሎ በሁለቱ አገራት በትራንስፖርት ሚኒስትር የሚመራ የልዑካን ቡድን ከሚመለከታቸው የጅቡቲ ወገን ጋር ጅቡቲ ላይ ተገናኝተው የወደብ አጠቃቀም ስምምነቱን በአግባቡ ሊተገበር የሚችልበትን ሥርዓት በመዘርጋት ችግሩን ለማስወገድና በሁለቱ አገራት የወደብ አጠቃቀም ስምምነት አንቀጽ 5 /4/ ላይ የተገለፀው የድህረ ክፍያ አገልግሎት እንዲቀጥል በጋራ ለመሠራት ስምምነቱ ላይ ደርሰዋል፡፡

በጋራ ስምምነቱ መሰረት የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ በወደብ አጠቃቀም ስምምነቱ በተጠቀሰዉ ጊዜ መክፈል ከማስቻል በዘለለ ወደፊት እንዲህ ዓይነቱ ችግር እንዳይከሰት የወደብ አጠቃቀም ስምምነቱን በአግባቡ ለመተግበር የሚያስችል ሥርዓትን መዘርጋት አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም ሥርዓቱን ለመዘርጋት የሚያስችሉ የተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶች ተደርገው በሁለቱ አገራት የወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሠረት የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት እናተዛማጅ የባሕር ወደብ አገልግሎት ክፍያን ተግባራዊ ለማድረግና የሚመለከታቸው አካላትን ሃላፊነትና ተግባር ለመወሰን የሚያስችል  አገራዊ መመሪያ በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18/ለ/ ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ትራንስፖርት ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባህር ወደብ ክፍያን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 315/2013 ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

2.1. **"ስምምነት"** ማለት እ.ኤ.አ. በአኘሪል 13/2002 በኢትዮጵያና ጅቡቲ የወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ የተፈረመ ስምምነት ነው፣

2.2. **"ዕቃ አስተላላፊ ወይም ዕቃ አስተላላፊ ድርጅት"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 እና ደንቡን ተከትሎ በወጣዉ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት በዕቃ አስተላላፊነት ለመስራት የዕቃ አስተላላፊነት የብቃት ማረጋገጫ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት ነው፣

2.3. **'ተዛማጅ የወደብ አገልግሎቶች ክፍያ'** ማለት የገቢና የወጪ እቃዎችን በተመለከተ በወደብ ላይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ሲሆኑ የወደብ ግብር /Port Dues/ ፤የመጋዘን ኪራይ /Storage Rent/፤ የሾር ሃንድሊንግ፤ዕቃን በኮንቴነር ዉስጥ የማሸግና የማዉጣት /Staffing and unstaffing/ እና የመሰሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

2.4. **"መነሻ የውል ሰነድ"** ማለት በጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊና በኢትዩጵየ ዕቃ አስተላላፊ መሃል በሚደረግ ስምምነት የሁለቱን ተዋዋይ ወገኖች ተነፃፃሪ መብትና ግዴት ያካተተ ሰነድ ነው፣

2.5. **'የፑል የብር ሂሳብ እና የፑል የውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ማለት'** በጅቡቲ ወደብ በጅቡቲ እቃ አስተላላፊ ለተሰጠ እቃ የማስተላለፍና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም እንዲቻል በንግድ ባንክ የሚከፈት ሂሳብ ነው፡፡

2.6. **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያበቃ የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች ፣ የቢሮ አደረጃጀት ፣

የካፒታል መሟላቱን እንዲሁም በዘርፉ የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ያሠራር ሥርዓት ለቀበል እና ለመተግበር ያለዉን ዝግጅት መኖሩን በማረጋገጥ በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የሚሰጥ ማስረጃ ነው፣

2.7. **'ንግድ ባንክ'** ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በባንክ የንግድ ዘርፍ እንዲሰማራ ፍቃድ የተሰጠው በአገሪቷ የሚገኝ የመንግስት ወይም የግል የንግድ ባንክ ነው፣

2.8. **'የባንክ ፈቃድ'** ማለት ማንኛውም አስመጪ ዕቃዎችን ከውጭ ሀገር በመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ እና ሌሎችንም ድጋፍ የሚያገኝበት ማስረጃ ነዉ፣

2.9. **'የትራንዚት ፍቃድ'** ማለት ዕቃው ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ለመላክ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወይም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚሰጠዉ ዕዉቅና መሠረት የባሕር ወደብ ባለቤት ከሆነዉ አገር ተመሳሳይ መ/ቤት የሚገኝ ፈቃድ ነው፡፡

2.10. **'አዋጅ'** ማለት የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 ነው፣

2.11. **'ባለሥልጣን'** ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፣

2.12. **'ሚኒስቴር'** ወይም **'ሚኒስትር'** ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

ይህ መመሪያ በዋናነት በጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊዎች በኩል የኢትዮጵያ ዕቃ አስተላላፊዎችን በመወከል የተሰጠውን የዕቃ ማስተላላፍና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎቶች በተመለከተ የሚጠየቅ ክፍያን በወደብ አጠቃቀም ስምምነት እና በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የውል ሰነድ ላይ በተገለፀው ጊዜ ማስፈፀም ነዉ፡፡

## 4. <u>አስፈጻሚ አካል</u>

በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣ 9 ሥር በተደነገገው መሠረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ‹‹የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የባህር ወደብ ክፍያን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/ 2006›› የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈፃሚነት የሚኖረው በጅቡቲ ወገን በድህረ ክፍያ የትራንዚት አገልግሎት ሥርዓት በአገኙት ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶችና በንግድ ባንኮች ላይ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 6. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ሚኒስቴሩ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

6.1 የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ በወደብ አጠቃቀም ስምምነት መሠረት እንዲተገበር የሚመለከታቸውን አካላትን ያስተባብራል ፡፡

6.2 ከባለሥልጣኑ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት በዚህ መመሪያ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት የማይወጡ ተቋማት ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

6.3 የወደብ አጠቃቀም ስምምነቱን በመደገፍ ስራ ላይ የዋሉ ሥርዓቶችን አተገባበር በተመለከተ በሚቀርብለት የአፈጻጸም ሪፖርት መሰረት ተገቢውን ማስተካከያ መመሪያ ይሰጣል፡፡

## 7. የዕቃ አስተላላፊ ድርጅት ተግባርና ኃላፊነት

ይህን መመሪያ በተመለከተ በዕቃ ማስተላለፍ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት የሚኖረዉ ሲሆን ከንዑስ አንቀጽ 7.1 እስከ 7.9 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸዉ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ላገኙ ዕቃዎች ሲሆን ከንዑስ አንቀጽ 7.10 እስከ 7.18 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸዉ ከባንክ ፍቃድ ዉጭ ለሚገቡ ዕቃዎች በተመለከተ ይሆናል፡-

7.1 የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ከጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ ድርጅት ለማግኘት ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው መነሻ የውል ሠነድ ላይ የተገለጹትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ባካተተ መልኩ የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ውል መዋዋል ይኖርበታል፣

7.2 በ7.1 ላይ የተገለፀው የተሟላ የዕቃ ማስተላላፍና ተዛማጅ አገልግሎቶች ውል ዋና ቅጅ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፣

7.3 በጅቡቲ ወገን ለተሰጠው የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያዉን በወቅቱ ለጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ በውሉ መሰረት ይፈጽማል ፣

7.4 ከጀቡቲ ወገን የሚቀርብ የትራንዚት አገልግሎት የተሰጠበት የክፍያ ሠነድ (Invoice) ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣ ትክክለኛነቱን ሲያረጋግጥ የክፍያ ሰነዱን (Invoice) የክፍያ አገልግሎት ለሚሰጠው ባንክ ያቀርባል፡፡

7.5 የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት የክፍያ ሠነድ (Invoice) ትክክለኛ ካልሆነ መከፈል ያለበትን የክፍያ መጠን በመግልፅ አገልሎቱን ለሰጠው የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ ማሳወቅ አለበት፣

7.6 በጅቡቲ ወደብ ለተሰጠ የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ ለንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ጥያቄው በቀረበ በ7 ቀናት ውስጥ ካልተፈቀደ ለብሄራዊ ባንክ እና በግልባጭ ለባለስልጣን መ/ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል ፣

7.7 የገቢ ዕቃ ለማጓጓዝ ከጂቡቲ አጓጓዥ /ትራንስፖርተርን/ ጋር የሚዋዋል ማንኛዉም ዕቃ አስተላላፊ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ FXD/14/2000 ላይ በተገለጸዉ መሠረት አጓጓዡ /ትራንስፖርተሩ/ የአገልግሎት ክፍያዉን በዉጭ ምንዛሪ እንዲያገኝ የሚያስችለዉን ለንግድ ባንክ መቅረብ የሚገባዉን ሠነድ /invoice/ ያቀርባል፤ ክፍያዉም ለአጓጓዡ /ለትራንስፖርተሩ/ እንዲፈጸም ይጠይቃል፣

7.8 ለገቢ ዕቃዎች የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀም አገልግሎቱ ለሚሰጠው ንግድ ባንክ ማመልከቻ ሲያቀርብ የሚከተሉትን ሠነዶች ማቅረብ አለበት፡-

   7.8.1 የውጭ ምንዛሪ ጥያቄ ማመልከቻ፣
   7.8.2 የትራንዚትና የወደብ አገልግሎት ኢንቮይስ (transit and port service invoice)
   7.8.3 የአቅራቢዎች ኡንቮይስ (Final suppliers invoce)
   7.8.4 ትራንዚት የተፈቀደብት ዲክላሬሽን ማለትም ዕቃው ከጅቡቲ እንዲመጣ በጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ የተመዘገበና ትራንዚት የተፈቀደበት የክሊሪንስ ዲክላሬሽን፣

7.8.5 የትራንዚት ዲክላሬሽን፣

7.8.6 የገቢ ዕቃ ባንክ ፈቃድ፣

7.8.7 የማስጫኛ ሠነድ ናቸው፣

7.9 ለወጪ ዕቃዎች የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀም አገልግሎቱ ለሚሰጠው ንግድ ባንክ መጠይቅ ሲቀርብ የሚከተሉትን ሠነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

7.9.1 የወጭ ምንዛሪ ማመልከቻ፣

7.9.2 የትራንዚትና ወደብ አገልግሎት ኢንቮይስ፣

7.9.3 የማስጫኛ ሠነድ፣

7.9.4 የኤክስፖርት ትራንዚት ዲክላሬሽን፣

7.9.5 የውጭ ዕቃ የባንክ ፈቃድ ናቸዉ

7.10 ሀገር ውስጥ ከሚገኙ የንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ለማይጠየቅባቸው የገቢ ዕቃዎችን የማስተላለፍ ሥራ ሲያከናውን በቅድሚያ የወደብ ሥነ-ሥርዓት ለማስፈጸም የሚያገለግል ሰነድ ሥራዉን እንዲከናዉንለት ከመረጠዉ አስመጪ ላይ ይቀበላል፣

7.11 በተቀበለዉ ሠነድ መሠረት ለትራንዚት አገልግሎት የሚያስፈልገዉን ወጪ በቅድመ-ትመና አሠራር በመተመን ለአስመጪዉ ያሳዉቃል፣

7.12 በቅድመ-ትመናው መሰረት  የውጭ ምንዛሬ መግዣ ተመጣጣኝ ገንዘብ /ብር/ ለዚሁ ተብሎ በሚከፈተው የፑል ሂሳብ  ያስገባል ፣

7.13 በጅቡቲ የዕቃ ማስተላላፍ አገልግሎት ለመስጠት ውል የተዋዋለው ዕቃ አስተላላፊ በውሉ መሰረት የሚጠበቅበት ተግባር በማከናወን የወደብ ክፍያዎችንና ተዛማጅ ክፍያዎችን የፈፀመበትን ሰነድ /invoice/ ሲልክለት በሶስት /3/ ቀን ጊዜ ውስጥ በማመሳከር ችግር የሌለበት መሆኑን ያረጋግጣል፣

7.14 በንዑስ አንቀጽ 7.13 መሰረት የተላኩት የክፍያ ሰነዶች /invoice/ ችግር ያለበት መሆኑ ከተለየ ለጅቡቲ ወኪሉ ችግሩን እንዲስተካከል ያሳውቃል፡፡

7.15 ዕቃ አስተላላፊው የተሟላ ሰነድ አቅርቦ እና ለትራንዚት አገልግሎት የሚውል በቂ ገንዘብ በደንበኛው ባንክ የትራዚት አገልግሎት የገንዘብ የፑል ሂሳብ ውስጥ አስቀምጦ /አሳግዶ/ የትራዚት አገልግሎት ክፍያ እንዲፈፀምለት ለባንኩ ጥያቄ በአቀረበ በአምስት /5/ የስራ ቀናት ውስጥ ለጅቡቲ ወኪሉ በዉጭ ምንዛሬ

የአገልግሎት ክፍያዉ ተላልፎ መረጃ ካልተሰጠው ጉዳዩ እንዲታይለት ለብሔራዊ ባንክ እና ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ያደርጋል /ያመለክታል/፣

7.16 በጅቡቲ የዕቃ ማስተላላፍ አገልግሎት ለሰጠው ዕቃ አስተላላፊ የአገልግሎት ክፍያዉ መተላለፉን የሚገልጽ ከባንክ የተገኘን መረጃውን በማያየዝ ለጅቡቲ ወኪሉ ያሳውቃል፣

7.17 ዕቃ አስተላላፊው ድርጅት ከባንክ ፍቃድ ውጪ የሚገቡ ዕቃዎችን ሲያስተላልፍ ከኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የትራዚት ፍቃድ ሲጠይቅ ለትራዚት አገልግሎት የሚውል የውጭ ምንዛሪ ክፍያ ተመጣጣኝ ገንዘብ በደንበኛው ንግድ ባንክ ማስገባቱን /ማሳገዱን/ የሚያረጋግጥ ሰነድ አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፣

7.18 የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎቶችና ክፍያ በተመለከተ የሚያከናውነውን ተግባር የሚገልጽ ሪፖርት ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴ አማካይነት ለባለሰልጣኑ ያስተላልፋል፣

## 8. <u>የንግድ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ይህን መመሪያ በተመለከተ የንግድ ባንክ የሚከተለው ተግባር እና ኃላፊነት የሚኖረዉ ሲሆን ከንዑስ አንቀጽ 8.1 እስከ 8.6 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸዉ ሀገር ውስጥ ከሚገኙ ንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ላገኙ ዕቃዎች ሲሆን ከንዑስ አንቀጽ 8.7. እስከ 8.10 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸዉ በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ለማያገኙ ዕቃዎች ይሆናል፡-

8.1 የዕቃ ማስተላላፍ አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል በዕቃ አስተላላፊ ድርጅት ሲጠየቅ ጥያቄው በቀረበለት በሰባት /7/ ቀናት ውስጥ ክፍያውን አገልግሎቱን ለሰጠዉ የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ ክፍያዉን በውጭ ምንዛሪ ያስተላልፋል፣

8.2 ለዕቃ ማስተላላፍ እና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎት ክፍያን ለመፈጸም በባንክ በኩል ከዕቃ አስተላላፊው የሚጠየቁ የተለያዩ ሠነዶች ቀደም ሲል ይሠራበት በነበረው መመሪያ FXD/07/1998 ላይ የተጠቀሱትን ሳይሆን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7.9 እና 7.10 ላይ የተዘረዘሩትን ብቻ መሆናቸዉን አዉቆ ይህንኑ ይተገብራል ፣

8.3 በቁጥር ውምክሪአዳ/014/2014 በጥር 20/2006 ዓ.ም በብሔራዊ ባንክ ለሁሉም ንግድ ባንኮች ባስተላለፈው ሰርኩላር እና በዚህ መመሪያ መሠረት ማንኛውም ባንክ የዕቃ ማስተላላፍ አገልግሎት ክፍያ ጥያቄን ዕቃ አስተላላፊው ማሟላት የሚገባው ሠነድ እና ገንዘብ መጠን እስካሟላ ድረስ ክፍያውን ቅድሚያ በመስጠት ያስተናግዳል፣

8.4 የዕቃ ማስተላለፍና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎት ክፍያ ጥያቄ ከዕቃ አስተላላፊዎች ሲቀርብለት የኢንቮይሱን ትክክለኛነት አረጋግጦ ክፍያ ይፈጽማል፣

8.5 የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ ጥያቄ ያቀረበ ዕቃ አሰተላላፊ ባንኩ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8.3 ላይ በተገለፀው መሠረት ለክፍያ የሚውል የውጭ ምንዛሪ አዘጋጅቶ እያለ በአንፃሩ ዕቃ አስተላላፊው የውጭ ምንዛሪውን መግዣ ተመጣጠኝ ብር ማቅረብ ካልቻለ ጉዳዩን በዋናነት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ በግልባጭ ለበሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፣

8.6 የአገሪቷን የገቢ እና የወጪ ዕቃ በማጓጓዝ ተግባር ላይ የጂቡቲ አጓጓዥ /ትራንስፖርተር/ ከዕቃ አስተላላፊዉ ጋር የሥራ ዉል ገብቶ አገልግሎት ሲሰጥ ከዕቃ አስተላላፊዉ በሚቀርብለት ሠነድ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ FXD/14/2000 መሰረት በ 7 ቀናት ዉስጥ ለጂቡቲ አጓጓዡ የአገልግሎቱን ክፍያ በዉጭ ምንዛሪ ይፈጽማል፡፡

8.7 ማንኛውም ንግድ ባንክ ከሀገር ውስጥ የንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ላልተሰጣቸው ዕቃዎች /Franco valuta & Others/ የዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ በቅድመ-ትመና አሰራር ለመፈፀም እንዲቻል ለትንዚት አገልግሎት ክፍያ የሚውል የፑል የገንዘብ እና የዉጭ ምንዛሪ ሂሳብ ያዘጋጃል፣

8.8 በቅድመ-ትመናው መሰረት ዕቃ አስተላላፊዉ ድርጅት ለዕቃ ማስተላለፍ አገልግሎት ክፍያ የሚውል የውጭ ምንዛሬ መግዣ ገንዘብ (ብር) በተከፈተው የፑል የገንዘብ ሂሳብ ውስጥ ሲያስገባ ንግድ ባንኩ የገንዘቡን ተመጣጣኝ የውጭ ምንዛሪ በውጭ ምንዛሪ ፑል ሂሣብ ውስጥ ያስገባል፣

8.9 የቀረቡት የክፍያ ሰነዶች /invoice/ የተሟሉና ችግር የሌለባቸው መሆናቸውን ከተረጋገጠ ዕቃ አስተላላፊው ለትራንዚት አገልግሎት ክፍያ ከአስቀምጠው /ከአሳገደው/ የገንዘብ የፑል ሂሳብ ላይ በመቀነስ ባንኩ ለዚሁ አገልግሎት

ከከፈተው የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ላይ ተመጣጣኝ የውጭ ምንዛሪ ክፍያ አገልግሎቱን ለሰጠው የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ ይከፍላል፣

8.10 በንዑስ አንቀጽ 8.9 ላይ የተደነገገውን እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ አስተላላፊው የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ ያስገባው /ያሳገደው/ ገንዘብ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ገንዘቡን በሶስት ቀናት እንዲያሟላ ያሳውቃል በተጠቀሰው ቀን ውስጥ ዕቃ አስተላላፊዉ ድርጅት ገንዘቡን ሚሟላት ካልቻለ ይህንኑ ለባስልጣኑ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 9. <u>የብሔራዊ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት</u>

ይህን መመሪያ በተመለከተ በሔራዊ ባንክ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

9.1 የዕቃ ማስተላለፍ እና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎት ክፍያን ለመፈፀም ንግድ ባንከ ክፍያው እንዲፈፀምለት የጠየቀው ዕቃ አስተላላፊ ማቅረብ የሚገባቸውን ሠነዶችን በተመለከተ የወጣውን መመሪያ FXD/07/1998 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7.9 እና 7.10 መሠረት በመከለስ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሳውቃል፣

9.2 በዚህ መመሪያ መሰረት በአገሪቷ ዉስጥ የሚገኙ የንግድ ባንኮች ስራቸውን ማከናወናቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

9.3 የዕቃ ማስተላለፍ እና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎት ክፍያ በ7 ቀን ውስጥ ክፍያ የማይፈጽም ባንክን ፣ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ለማያስፈልጋቸው ዕቃዎች አስመልክቶ የተደነገገው ድንጋጌዎች የማይተግብር ንግድ ባንክ እና የጅቡቲ አጓጓዥ /ትራንስፖርተር/ ለሰጠው የማጓጓዣ አገልግሎት በብሔራዊ ባንክ መመሪያ FXD/14/2000 መሰረት ክፍያ በማይፈጽም የንግድ ባንክ ላይ ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

## 10.<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት</u>

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

10.1. ከባለሥልጣኑ በሚደርሰው የዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር በቀር ሌሎች በድንበር ዘለል የዕቃ ማስተላለፍ ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ በሚያደርገው ሥርዓት መሰረት ይከታተላል ፣ይቆጣጠራል፤

10.2. በሀገር ውስጥ ከንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ለማይጠየቅባቸው ገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ፈቃድ ለመስጠት ዕቃ አስተላላፊው የትራንዚት ፈቃድ ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲጠይቅ በንግድ ባንክ የትራንዚት አገልግሎት ክፍያ የገንዘብ ፑል ሂሳብ ውስጥ ገንዘቡ ማስገባቱን አረጋግጦ ፈቃድ ይሰጣል ፣

10.3. የዕቃ አስተላላፊው በዚህ መመሪያ እና በሌሎች መመሪያዎች ከተሰጡት ሃላፊነት ውጪ ህገወጥ ተግባር ላይ ተሰማርቶ ሲገኝ ለባለስልጣኑ እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል ፣

## 11.<u>የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ተግበርና ኃላፊነት</u>

ይህን መመሪያ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

11.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ላይ በተሰጠው ኃላፊነት በሚያደረገው ክትትልና በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት የዚህን መመሪያ አፈፃፀም እና አተገባበር ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

11.2 በሚያደረገው የቁጥጥርና የክትትል ሥራ በመመሪያው አተገባበር ላይ የተከሰተውን ችግር በመለየት አማራጭ የመፍትሄ ሃሣቦችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፣

11.3 በሁለቱ ሀገሮች ስምምነት አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በተቀመጠው መሠረት በዕቃ ማስተላለፍ እና ተዛማጅ የወደብ አገልግሎት ላይ በሚሰማሩ የኢትዮጵያ እና የጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊዎች መካከል የሚደረግ የውል ስምምነት እንዲከበር ከጅቡቲ አቻው ጋር በመመካከር ይሰራል፣

11.4 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8.1 መሠረት ኃላፊነቱን በአግባቡ ያልተወጣ ንግድ ባንክ ከዕቃ አስተላላፊ ድርጅት በሚቀረብለት ሪፖርትና መረጃ መሠረት ለብሔራዊ ባንክ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ያሳውቃል፣

11.5 ዕቃ አስተላላፊ ድርጅቱ ከጅቡቲ ዕቃ አስተላላፊ ጋር ያሰረውን የሥራ ውል ይመዘግባል በውሉ መሠረት የአገልገሎት ክፍያው መፈፀሙን በሚዘረጋዉ የዉስጥ አሠራር ይከታተላል፣

11.6 በዚህ መመሪያ እና በሌሎች መሰል የአሠራር ሥርዓቶች (መመሪያዎች) ለዕቃ አስተላላፊው የተሰጡ ሃላፊነትና ተግባራትን በአግባቡ በማይወጡ የዕቃ አስተላላፊዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

11.7 ከባለስልጣን መ/ቤቱ የድንበር ዘለል ዕቃ የማስተላለፍ ስራ እንዲሰሩ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውን ዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ለጂቡቲ ወደብ ባለሥልጣን፣ለንግድ ሚኒስቴር እንዲሁም ለሌሎች ለሚመለከታቸዉ አካላት ያስተላልፋል የተላለፈዉን ዝርዝር በየጊዜዉ ወቅታዊ ደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

### 12. መመሪያዉን ስለ ማሻሻል

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህ መመሪያ ሊሻሻል ይገባዋል ብሎ በአመነ ጊዜ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊያሻሽለዉ ይችላል ፡፡

### 13. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም**

**ወርቅነህ ገበየሁ**

**የትራንስፖርት ሚኒስትር**